# BBC LEARNING ENGLISH
# Essential English Conversation
## What's your favourite place?
## የ ምትወጅው/የ ምትወደውቦ ታ የ ቱ ነ ው?

BBC LEARNING ENGLISH እንግሊዝኛ መማር

*This is not a word-for-word transcript*

**ምህረት**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊተዋቸው የማይቻላቸውን የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation በደህና መጡ። ምህረትእባላለሁ። በዚህ ክፍል በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ በጣም ስለሚወዱት ቦታ እንዴት መናገር እንደሚቻል ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች ስለሚወዷቸው ቦታዎች ሲያወሩ ያዳምጡ።

**Sian**
*Hi Phil, what's your favourite place?*

**Phil**
*My favourite place is the market. How about you?*

**Sian**
*Mine is the restaurant.*

**ምህረት**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን። የመጀመሪያዋ ተናጋሪ 'የምትወደው ቦታ የትኛው ነው?' 'What's your favourite place?' በማለት ነው የጠየቀችው። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*What's your favourite place?*

**ምህረት**
ሁለተኛው ተናጋሪ የሚወደው/የሚመርጠው 'favourite' ቦታ ገበያው 'market' እንደሆነ መልሶላታል። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይናገሩ።

*My favourite place is the market.*

**ምህረት**
ከዚያም የመጀመሪያዋን ተናጋሪ ተመሳሳይ ጥያቄ ጠየቃት። አንድ ሰው የጠየቀዎትን ጥያቄ እራሱን እንዲመልስልዎት ከፈለጉ 'አንችስ/አንተስ?' 'How about you?' በማለት መጠየቅ ይችላሉ። ያዳምጡና ሐርጉን ደግመው ይበሉ።

*How about you?*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ምህረት**
ስለምንወዳቸው ቦታዎች እያወራን እንዳለን ስለምናውቅ የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ደግሞ ‘የምወደው/የምመርጠው ቦታ’ ‘My favourite place…’ ማለት አልተጠበቀባትም። እንዲሁ ብቻ ‘የእኔ’ ‘mine’ ‘ምግብ ቤቱ’ ‘restaurant’ ነው ብላለች። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Mine is the restaurant.*

**ምህረት**
በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች ስለሚወዷቸው ስፍራዎች ሲያወሩ በማዳምጥ እርስዎ ያሉትን ይፈትሹ።
ማርክ ‘የመናፈሻ ስፍራውን’ ‘park’ ይወዳል፤ ፒት ደግሞ ‘ወንዙን’ ‘river’ይመርጣል።

*Hi Mark, what’s your favourite place?*

*My favourite place is the park. How about you?*

*Mine is the river.*

አሊስ የፖስታ ቤቱን ‘የመዋኛ ገንዳ’ ‘swimming pool’ ትወዳለች። የክሌር ተመራጭ ቦታ ደግሞ ‘ሲኒማ ቤቱ’ ‘cinema’ ነው።

*Hi Alice, what’s your favourite place?*

*My favourite place is the swimming pool.*

*Mine is the cinema.*

**ምህረት**
እሺ፥ አሁን ደግመን እንሞክር። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሩን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ይሰሟቸዋል።

*What’s your favourite place?*
*What’s your favourite place?*

*My favourite place is the market.*
*My favourite place is the market.*

*How about you?*
*How about you?*

*Mine is the restaurant.*
*Mine is the restaurant.*

**ምህረት**
በጣም ጥሩ! እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱት እንመልከት። አረፍተ ነገራቱን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይናገሩ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*ከሁሉ አስበልጠህ የምትወደው ቦታ የትኛው ነው?*
*What's your favourite place?*

*እኔ የምወደው ገበያውን ነው።*
*My favourite place is the market.*

*አንችስ?*
*How about you?*

*እኔ ምግብ ቤቱን ነው።*
*Mine is the restaurant.*

**ምህረት**
በጣም ጥሩ፤ እሽ አሁን በእንግሊዝኛ ስለቦታዎች መጠየቅ እና መመለስ እንደሚቻል አውቀዋል። ለመጀመሪያው ተናጋሪ ምላሽ በመስጠት፥ አቅጣጫ እየጠየቁ ልምምድ ያድርጉ።

*What's your favourite place?*
*Mine is the restaurant.*

**ምህረት**
በጣም ጥሩ፤ አሁን መልስዎን ለማመሳከር ጠቅላላውን ውይይት እንደገና ያዳምጡ።

***Sian***
*Hi Phil, what's your favourite place?*

***Phil***
*My favourite place is the market. How about you?*

***Sian***
*Mine is the restaurant.*

**ምህረት**
በጣም ጥሩ። አሁን በእንግሊዝኛ በሚኖሩበት ከተማ ስለሚወዱት ቦታ መጠየቅ እና መናገር ይችላሉ። የተማሩትን መለማምድን ያስታውሱ። ጓደኛ ይፈልጉና ስማችሁን መጠየቅና መናገርን ይለማመዱ። ለተጨማሪ የEssential English Conversation ዝግጅቶች በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። ደህና ይሁኑ!


© British Broadcasting Corporation 2018